# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

4

★ ጭቁን ሴቶችና ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት

★ ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር

★ የቦልሼቪክ ፓርቲ አጭር ታሪክ

★ ጩኸቴን ቀሙኝ ፡

★ ለነማርክስ ፍልስፍና አጭር መግቢያ

ሰኔ ፲፭ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ.ም.

**ለውይይት መነሻ**

አብዮታዊት ኢትዮጵያ ከቍጥር ፩ ጀምራ «ለነማርክስ ፍልስፍና አጭር መግቢያ» በሚል ርእስ ሥር በተከታታይ ትምህርታዊ የሆኑ የፍልስፍና ጽሑፎች ታቀርባለች ። እነዚህ ጽሑፎች የማርክሲዝምን ርእዮተ ዓለም ገና ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚተዋወቁ የውይይት ክበቦች መነሻ ሃሳቦች እንደሚሰጡ ሆነው የቀረቡ ናቸው ።

# ለነማርክስ ፍልስፍና አጭር መግቢያ

ከን. ዓ.

በአገራችን « መፈላሰፍ » የሚለው ቃል ለሁሉም ሰው አንድ ዓይነት ትርጓሜ አይኖረውም ። አንድ ሰውም እንኳ ቢሆን ቃሉን በተለያየ ጊዜ ሲጠቀምበት የተለያየ መልእክትን ለማስተላለፍ ፈልጐ ይሆናል ። አንዳንዴ « አስተዋይ ፤ ብልህ ፤ አዋቂና ባለአእምሮ » መሆንን ለማመልከት ፤ አንዳንዴ « መናኝ ፤ መነኩሴና . . ወዘተ » መሆንን ለመጠቆም ፤ አንዳንዴም በማይሆንና በማይመስል ጉዳይ ላይ « አጉል መራቀቅን » ለማሳየት ይሆናል ።

በዚህ መሠረት እንግዲህ አንዳንድ ሰዎች ሲናገሩ « እገሌ ይፈላሰፋል » ያሉ እንደሆነ ያን ቋሸሹ ይመስላቸዋል ። ብዙውን ጊዜ አንድ ሰው « ይፈላሰፋል » ሲባል ዝም ብሎ ለዕለታዊ ኑሮው ምንም ዓይነት ጠቀሜታም ሆነ መመሪያ በማይሰጡትና አጉል በተራቀቁ ጥያቄዎች / ሃሳቦች / አንጐሉን ይበጠብጣል ለማለት ነው ።

ባጭሩ ፍልስፍና በአንዳንድ ሰዎች አስተያየት በማይጨበጡ ረቂቅ ነገሮች አንጐልን እንደመበጥበጥ ይቆጠራል ። እንደዚህም አንጐል ተበጥብጦ አንድ ሰው ራሱ ለሚጠይቃቸው ጥያቄዎች መልስ ቢያገኝም ቢበዛ ዕውቀቱን ያዳብራል እንጂ ይህ ሰው ተፈላስፎ ያገኛቸው ነገሮች ኑሮ ለሚያቀርባቸው ችግሮች መፍትሔ ሊሰጡ አይችሉም ።

የመፈላሰፍ ዓላማው መች ኑሮን ለመኖር ሆነና ። በፊውዳሉ ርእዮተ ዓለም እንደሆነ መዝገበ ቃላቱ መፈላሰፍን ጨርሶ ከመመነንና ከኑሮ እንደመውጣት ይቆጥረዋል ። ወይ መኖር ወይ ነገር ዓለሙን ትቶ መፈላሰፍ ። የቃሉም የራሱ አመጣጥ የሚያመለክተው ይህንኑ ነው ። ፊሎሰፍያ ማለት ከሁለት የግሪክ ቃላት የተገጣጠመ ነው ። ፊሎ ማለት ዕውቀት ማለት ነው ። ሰፊያ ደግሞ ፍቅር ማለት ነው ።

አንባቢ « ለመመነን አልፈልግም አልፈላሰፍም » ብሎ እንደማይል ተስፋ አለን ። ይቺን ጽሑፍ የሚያነበው ምናኔ ለመግባት ሳይሆን ስለ ተጨባጩ ኑሮው ፤ ስለኅብረተሰባችን ችግሮች ስለጭቆና ፤ ስለአብዮት ለመረዳት ፤ የራሱንና የኅብረተሰቡን ኑሮ ይበልጥ የተሟላ ለማድረግ በሚደረገው ትግል ሆን ብሎ ለመሳተፍ ከሆነ ትንሽ ርዳታ ያገኝበታል ብለን እንገምታለን ። ይቺ ጽሑፍ ስለማርክስ ፍልስፍና በጣም ባጭሩ አንዳንድ መሠረታዊ ነገሮችን ታስረዳለች ። የማርክስ ፍልስፍና ደግሞ የመናኝ ፍልስፍና አይደለም ። ለታጋዮች መመሪያ ፤ ለትግል ፋና የሚሰጥ ብርሃን እንጂ ።

ፍልስፍና ፤ ፍልስፍና ነው ። የማርክስም ቢሆን አንጐልን መበጥበጥ አይደለም ወይ ? ለዚያውስ ርባን ለሌለው ነገር ? ብሎ አንባቢ ሊጠይቅ ይችላል ። መልሳችን አጭር ነው ። የማርክስ ፍልስፍና እነዚህን የተሳሳቱ ሁለት ግምቶች አፈራርሶ የሚጥል አብዮታዊ ፍልስፍና ነው ።

እርግጥ ነው የቡርዧ ፈላስፋዎች ያው እንደነሱው ፍልስፍና የማይጨበጥና የማይደረስበት ነገር አድርገው ለማቅረብ ይሞክራሉ ። ይሸፋፍኑታል ። « ያስደነግጥልናል » የሚሉትን ነጥብ ብቻ ነጥለው ወስደው ሰፊውን ሕዝብ ያስፈራሩበታል ። ነገር ግን የማርክስ ፍልስፍና መሠረታዊ ሃሳቦች ከሁላችንም ዕለታዊ ኑሮ ጋር በጣም የተያያዙና በየዕለቱ የሚያጋጥሙን ተጨባጭ ሀቆች ስለሆኑ በጣም ቀላል ሃሳቦች ናቸው ። ታዲያ ለምን ይኸ ሁሉ ማወናበድ ይደረጋል ? ታዲያ ለምን ይኸ ሁሉ የሰፊውን ሕዝብና የማርክስን ፍልስፍና ለማቆራረጥ ይሞከራል ? ይኸም በጣም ግልጽ ምክንያት አለው ። የማርክስ ፍልስፍና መሠረታዊ ሃሳቦች ጥረታቸው ከሥራ ላይ ሊውሉ የሚችሉ መመሪያዎችን ለታጋዩ ሕዝብ ለማስጨበጥ ነው ። «እስከ ዛሬ የነበሩት ፈላስፋዎች ይላል» ማርክስ ራሱ «እስከ ዛሬ የነበሩት ፈላስፋዎች ሥራዬ ብለው ይዘውት የነበረው ዓለምን ለማወቅ ነበር ። ጥረቱ መሆን ያለበት ግን ዓለምን ለመለወጥም ነው ።»

እንግዲህ ተጨባጩና ከዕለታዊ ኑሮዋችን ጋር የተያያዘው የማርክስ ፍልስፍና ለዕውቀት ፍቅር ሲባል ብቻ የሚደከምበት ነገር አይደለም ። ለትግል ፤ ለለውጥ ፤ ለዕለታዊ ኑሮም የሚያገለግል መመሪያና መሣሪያ ነው ። ማርክስ እንደሚለው እንደዚህ ዓይነቶቹ ትክክለኛ አስተሳሰቦች በሚሊዮን በሚቆጠር ሕዝብ አእምሮ ሲታነጹ ምንም የማይበግራቸው የለውጥ ኃይሎች ይሆናሉ ።

ታዲያ እንዲህ ከሆነ በዝባዦች የማርክስ ፍልስፍና እተበዝባዥ ጆሮ እንዳይገባ ቢጥሩ ፤ በዚህም እነሱ ከተወለድንበት ቀን አንስቶ እስከ ዕለተ ሞታችን ድረስ ካቀራኙን ፍልስፍናቸው እንዳንላቀቅ ቢደክሙ ምን ያስደንቃል ?

አንባቢ ፤ እኔ / ፍልስፍና የለኝም ነበር / ገና « ፍልስፍናን ለማወቅ » ነው ይቺን « ጋዜጣ » የገዛሁት ። « ታዲያ ሕይወትህን ሙሉ ፍልስፍናቸውን ታቅፈህ ኖረሀል የምባልባት ፈሊጥ ምንድን ነው ? » ብሎ ይጠይቅ ይሆናል ። ቀጥሎም « እኔ በሕይወቴም ተፈላስፌ አላውቅም ። እንኳን የሰው ፍልስፍና ልቀበል / ልታቀፍ / ይቅርና የራሴም ፍልስፍና የለኝ » ይል ይሆናል ።

ግን እስቲ ፍልስፍና የለው እንደሁ ለመመልከት አንዳንድ ቀላል ጥያቄዎችን እናንሳ ። ሰው ከየት መጣ ? የሰው ልጅ የወደፊት ዕድል እንዴት ይሆን ?

ሰው ሆና አንድ ቀን ራሱን በእነዚህ ጥያቄዎች ያላስጨነቀ ያለ አይመስለንም ። በነዚህ ጥያቄዎች ላይ ሁሉም ራሱን አስጨንቋል ። ሁሉም ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ ሰጥቷል ። አንዱ ሰው ሀብታም ሌላው ሰው ድሀ ለምን ይሆናል ? በሚለው ጥያቄ ሁሉም ሰው ይመልሳል ። በሀገራችን እብዛኛው ሰው ለዚህ ሲመልስ ሀብታምና ድሀ « የአርባ ቀን ዕድል ነው » « ይታደሏል እንጂ መች ይታገሏል » ይላል ። ይህ ራሱ እንግዲህ አንድ ዓይነት ፍልስፍና ነው ። ለዚሁ ጥያቄ ደግሞ ሌላ መልስ አለ ። የሁብታምና የድሀ ጥያቄ ሲነሳ «የምን የአርባ ቀን ዕድል ጉዳይ. . . እንዲህ ያለ ነገር የለም. . . ይታገሏል እንጂ መቼ ይታደሏል » የሚሉ አሉ ። ይኸ ደግሞ ጨርሶ የፊተኛው ታቃራኒ የሆነ ሌላ ፍልስፍና ነው ።

ማንም ሰው ፍልስፍና የለኝም ሊል ይችል የነበረው እነዚህ ጥያቄዎች ሲጠየቁ « አላውቅም አልመልስም » ቢል ነበር ። ግን አይልም ። በሀገራችን እስካሁን ነግሦ የቆየው ድህነትን የአርባ ቀን ዕድል ጉዳይ አድርጐ የሚያየው ፍልስፍና ነው ። ይህ ደግሞ በአጋጣሚ አይደለም ። እንዲህ ዓይነቱ ፍልስፍና በድህነት የሚኖሩ ሰዎች ድህነትን ለማሸነፍ ከመታገል ይልቅ « የዕድላቸውን » ተቀብለው እንዲቀመጡ ያደርጋቸዋል ። በትግል አያምኑም ። ስለዚህ በዝባዦች ብዝበዛቸውን ሊቀጥሉ ይችላሉ ማለት ነው ። ስለዚህ በኅብረተሰባችን ውስጥ በዝባዦች ይህንን ፍልስፍና ከልጅነታችን ጀምረው ሊቀርጹብን ይሞክራሉ ። ከኛም ጋር ተዋህዶ ያድጋል ። ለዚህ ነው ሕይወታችንን ሙሉ የነሱን ፍልስፍና ታቅፈን እንድንኖር ጥረት ያደርጋሉ ያልነው ።

በሌላ በኩል ግን « ይታገሏል እንጂ መች ይታደሏል » የሚልው ፤ በአርባ ቀን ዕድል የማያምነው ፍልስፍና ለበዝባዦች አይመችም ። ምክንያቱም ድህነትና ሀብታምነት የዕድል ጉዳይ ሳይሆን የትግል ጉዳይ ነው ስለሚል ድሆች ወይም ተበዝባዦች ዕድላቸውን ማማረር ትተው ፤ ሀብታምና ድሀ የሚሉት ክፍፍል ሰውና ታሪክ ያመጣው ነገር መሆኑን ተገንዝበው እንዲታገሉና ሁኔታቸውን እንዲለውጡ ይጋብዛቸዋል ማለት ነው ።

ስለዚህ በዝባዦች « አትፈላሰፉ » ሲሉ « እኛ የሰጠናችሁ ፤ ከልጅነት ጀምሮ የቀረጽንባችሁ ፍልስፍና አለ ፤ እሱን ይዛችሁ ኑሩ » ማለታቸው ነው ። የማርክስ ፍልስፍናም ጥረት ፍልስፍና ለሌላቸው ሰዎች ፍልስፍና «ለመስጠት» አይደለም አድኃሪዎች በሕዝቡ አዕምሮ የቀረጹትን ለትግል የማይመች ፍልስፍናን አስወግዶ ሌላ ለትግል የሚያግዝ ፍልስፍና በሕዝቡ አዕምሮ ለመቅረጽ ነው ። የዚህን ተራማጅ ፍልስፍና ዋናነት ማርክስ ሲያስረዳ « እንዲህ ዓይነቱ ተራማጅ አስተሳሰብ በሚሊዮን በሚቆጠረው ሕዝብ አዕምሮ ሲታነጽ የማይበገር የለውጥ ሞተር ይሆናል » ይላል ።

# የማርክሲዝም ሌኒንዝም ፍልስፍና

## ዲያሌክቲካዊ ማቴሪያሊዝም /ቁስ አካልነት/

### ም ዕ ራ ፍ ፩

ይህ ፍልስፍና ዲያሌክቲካል ማቴርያሊዝም (ቁስ አካልነት) የተባለው ፍልስፍና ነው ። ይህ ምን ዓይነት ፍልስፍና እንደሆነ ለመረዳት በቅድሚያ ማቴርያሊዝም ምን እንደሆነ ከዚያም ዲያሌክቲክስ ምን እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል ፡፡

ግን መጀመሪያ እስቲ ፍልስፍና ራሱ ምንድን ነው ? ፍልስፍና ለአንዳንድ ሰፋፊና አጠቃላይ ለሆኑ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የሚደረግ ምርምር ማለት ነው ። ወይም ሁለትና ሁለት ስንት ነው ተብሎ ይህንን ለማግኘት የሚደረገውን ውጣ ውረድ አፍ ሞልቶ መፈላሰፍ ነው ማለት አይቻልም ። ይህ ካልተቻለ ታዲያ «እነዚህ ሰፋፊ ጥያቄዎች » የሚባሉት ምንድን ናቸው ? እነዚህ ጥያቄዎች ለምሳሌ እንደሚከተሉት ዓይነት ሊሆኑ ይችላሉ ።

ዓለም ከየት መጣች ? ተፈጥሮ ምንድን ነው መቼ «ተጀመረ » ? ማለቂያውስ ? ሰው ከየት መጣ መጨረሻውስ ምን ይሆን ? ሐሳብ ከየት ፈለቀ ? እነዚህን ሰፋፊ ጥያቄዎች ለመመለስ ማውጣትና ማውረድ መፈላሰፍ ይባላል ።

እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ሁሉም ሰው ይሞክራል ። ለጥያቄዎቹ ብዙ መልሶች አሉ ። ጥቃቅኖቹን ልዩነቶች ወደጐን ብንተዋቸው ከጥንት ጀምሮ ለነዚህ ጥያቄዎች በሚሰጡት መልሶች እየታዩ ፈላስፎች በሁለት ታላላቅ ክፍሎች ይከፈላሉ ። በአንድ በኩል በሳይንስና በዕውቀት ላይ የተመረኮዘ መልስ ለማግኘት የሚሞክሩ ክፍሎች አሉ ። በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህን ጥያቄዎች በዕውር እምነት ፤ በተጨባጭ ሳይንሳዊ ማስረጃ በማይረጋገጥና እንዲያውም ብዙውን ጊዜ ሳይንስ የሚያረጋግጣቸውን ሐቆች እንኳን ዓይናቸው እያየ የተፃረሩ መልሶች የሚሰጡ ክፍሎች አሉ ። በዚህ መልክ ፈላስፋዎችን በክፍል በክፍል ለመለየት አንድ መሠረታዊ ጥያቄ ይቀርባል ። ይኸውም የፍልስፍና ዋና ጥያቄ የተባለው ነው ። ይህ የፍልስፍና ዋና ጥያቄ ምንድን ነው ? ለዚህስ የሚሰጡት ሁለት ዓይነት መልሶች ምንድን ናቸው ? እነዚህን ተራ በተራ እንመልከት ።

## ፩· የፍልስፍና ዋና ጥያቄ ምንድን ነው ?

በአካባቢያችን ብዙ የተሰበጣጠሩ ነገሮች አሉ አንዳንዶቹ በድን ናቸው ። ሌሎቹ ይንቀሳቀሳሉ ። አንዳንዶቹ ይጨበጣሉ ፤ ይታያሉ ። ሌሎቹ አይጨበጡም ፤ አይታዩም ። በስፋትና በክብደት ከትንሿ አቧራ አንሥቶ «የሰማይ ስባሪ » እስከሚመስሉት ትላልቅ ነገሮች ፤ በርቀትና በቅርበት እጎናችን ካሉት ወንዞችና ተራሮች ለዓይን እስከሚያስቸግሩትና በመነጽር እስከሚደርስባቸው ከዋክብት በአካባቢያችን አሉ ። በነዚህ ላይ ደግሞ አካባቢያችን በአንዳንድ ክስተቶች ፊኖ ሚና ይታጀባል ። ክረምትና በጋን ፤ ብርሃንና ጨለማን የመሳሰሉም ክስተቶች አሉ ። መዝገበ ቃላቱ እነዚህን ሁሉ አጠቃልሎ ምልዓተ አካል ይላቸዋል ። «የሰማይ የምድር፤ የባሕር የፀሐይ የጨረቃ የጨለማ አካል ምልዓተ አካል ይባላል » ይላል ። ሰው ሆኖ ምን ጊዜም ቢሆን እነዚህ እጅግ የተሰበጣጠሩ ነገሮች ምንድን ናቸው ? እንደዚህስ ከተሰበጣጠሩ የሚያያዙበት ነገር አለ ወይ ? ብሎ ራሱን መጠየቁ አይቀርም ።

ሳይንስ እንደሚያስረዳን እነዚህ ሁሉ ነገሮች ሺህ ጊዜ የተሰበጣጠሩ ቢመስሉም አንድ የሚያስተሳሥራቸው ጠባይ አላቸው ። ይኸውም ማተር ወይም ቁስ አካል መሆናቸው ነው ። ቁስ አካል ናቸው የሚባለው እንዴት ነው ? ቁስ አካልነት አላቸው የሚባለው እነዚህ ሁሉ ነገሮች እኛ ፈለግናቸው አልፈለግናቸው ፤ ፈቀድናቸው አልፈቀድናቸው ፤ አየናቸው አላየናቸው ፤ ገቡን አልገቡን ከኛ ቁጥጥርና ከኛ ሕሊና ውጪ ያሉ ነገሮች መሆናቸው ነው ። እነዚህ ከሐሳብና ከሕሊና ውጪ ነባር ሆነው ፤ ነፃ ሆነው የሚገኙ ነገሮችን ሁሉ በአጠቃላይ ቁስ አካል ብለን እንጠራቸዋለን ።

ግን ሐሳብ ራሱስ ? መኖራቸው ሊካድ የማይቻል ከኛው ጋር አብረው ያሉ ሐሳብ ፤ ሕሊና፤ ፍቅር ፤ ጥላቻ ..... የመሳሰሉ ነገሮች አሉ ። ሳይንስ እንደሚያስተምረን ሐሳብና ቁስ አካል የተለያዩ ነገሮች ሳይሆኑ እጅግ የተያያዙ ነገሮች ናቸው ።

እንግዲህ ከጥንት ጀምሮ ሰዎች ራሳቸውን የሚያስጨንቁበት ጥያቄ አለ ። ከቁስ አካልና ከሐሳብ ማን ይቀድማል ? ማን የበላይነት አለው ? የሚል ነው ። የነማርክስን ፍልስፍና ቁስ አካላዊ (ማቴርያሊስት) ከሚያሰኘው ምክንያት አንዱ ከሐሳብ ቁስ አካል ይቀድማል ስለሚል ነው ። ሌላውን ሁለተኛው የፈላስፎች ሠፈር ደግሞ ሃሳባዊ ( አይዲያሊስት) የሚያሰኘው ከቁስ አካል ሐሳብ ይቀድማል ስለሚል ነው ። እስቲ እነዚህን ሁለት መልሶች ጠጋ ብለን እንመልከታቸው ።

## ፪. ለፍልስፍና ዋና ጥያቄ የሚሰጡት ሁለት መሠረታዊ መልሶች

ፈላስፋ ሲባል ለዚህ መሠረታዊ ጥያቄ በሚመልሰው እየታየ ለሁለት ይከፈላል ። ለዚህ ጥያቄ ሳይንሳዊ የሆነ መልስ የሚሰጡ ፈላስፎች በአንድ በኩል ሲቆሙ ሳይንሳዊ ያልሆነ መልስ የሚሰጡት ደግሞ በሌላ በኩል ይገኛሉ ።

በመጀመሪያ ሃሳባውያን ወይም አይዲያሊስት የሚባሉት አሉ ። የነዚህ ፈላስፎች እምነት ፤ ገና ሰዎች መመራመር ሲጀምሩ በሳይንስ አለመስፋፋት የተነሣ የተስፋፋ እምነት ነው ። ሃሳባውያን ሐሳብ ከቁስ አካል ይቀድማል ይላሉ ። አንዳንዶቹ እንዲያውም ነገሩን አለቅጥ ያከሩና ከሕሊና ውጪ ምንም ዓይነት ቁስ አካል የለም ይላሉ ። ፀሐይ ፤ ጨረቃ ፤ ድንጋይ ፤ አሉ ማለት የምንችለው በሕሊናችን ልንቀርፃቸው እስከምንችል ድረስ ብቻ ነው ። ከአንጎላችን ውጪ ሊኖሩ አይችሉም እስከ ማለት ይደርሳሉ ። በነዚህ ሰዎች አስተሳሰብ እንግዲህ አዲስ አበባ የተባለችውን ከተማ ላላያትና ለማያውቃት ሁሉ የለችም ማለት ነው ። በአጠቃላይ የዚህ ፍልስፍና መሠረታዊ እምነት ሐሳብ ከቁስ አካል ይቀድማል የሚል ነው ።

ይህም ማለት ከተራራው ፤ ከወንዙ ፤ ከሰው፤ ከፀሐይ .... በፊት ሐሳብ ወይም መንፈስ ለብቻው ያንዣብብ ነበር ማለት ነው ። ይህ አስተሳሰብ ዞሮ ዞሮ ከቁስ አካል በፊት አንድ የማይታይ ሐሳብ ነበር ይልና እንዲያውም እስከናካቴው ቁስ አካል የፈለቀው ከዚህ ረቂቅ ሐሳብ ተፈጥሮ ነው ብሎ ያስተምራል ። ከቁስ አካል ውጪ ፤ ከቁስ አካል በላይ ፤ ከቁስ አካል ቀደም የሆነ ሐሳብ አለ ይላል ።

ከዚህ ሌላ ፤ ቁስ አካለኞች ወይም ማቴሪያሊስቶች የሚባሉ አሉ ። እንደሚጠበቀው እነዚህ ደግሞ ለፍልስፍና መሠረታዊ መልስ ሲሰጡ የሃሳባውያንን አስተሳሰብ ሙሉ በሙሉ እየተቃረኑ ነው ። ቁስ አካል ከሐሳብ ይቀድማል ይላሉ ። እነዚያኞቹ ቁስ አካልን «የፈጠረው» ሐሳብ ነው የሚሉትን ሁሉ ይገለብጡና ሐሳብ የሚባለው ነገር የፈለቀው ቁስ አካል የሆነው አንጐል አድጐና እየተቀነባበረ ሔዶ አንድ ከፍተኛ ደረጃ ስለደረሰ ነው ይላሉ ። ሐሳብ የሌለው ቁስ አካል በየቀኑ የሚታይና ለመኖሩም ሳይንሳዊ ማረጋገጫ የሚገኝለት ነገር ነው ። ለምሳሌ እፊታችን የሚቀርበው እንጀራ አለ ። ለማረጋገጥ የፈለገ አንሥቶ ሊጐርሰውና እንጀራ የሚባለው ነገር ሲበላ የትም ቢሆን የሚያመጣውን የመመገብ ፤ ሆድ የመሙላት.... ጠባይ አይቶ ሊያረጋግጥ ይቻላል ። ነገር ግን ከቁስ አካል ውጪ ሐሳብ ብቻውን ሽርጉድ ሲል በእምነት ካልሆነ በስተቀር ሳይንሳዊ ማረጋገጫ እየሰጠ አየሁ የሚል ሰው የለም ።

እንግዲህ በነዚህ ፈላስፋዎች አስተሳሰብ እንኳን ከቁስ አካል በላይ ፤ ከቁስ አካል በፊት ይቅርና ከቁስ አካል ውጪ ብቻውን የሚቆም ምንም ነገር የለም ። እንግዲህ የማቴርያሊስቶች እምነት

በሚከተሉት ሦስት ዋና ዋና አስተሳሰቦች ሊያጠቃልሉ ይችላሉ ።

ሐሳብን የሚያፈልቀው ቁስ አካል ነው ። ቁስ አካል ከሐሳብ ውጪ ሊኖር ይችላል ። ሐሳብ ግን ለቁስ አካል ተቀጢላ እንደመሆኑ መጠን ከቁስ አካል ተለይቶ መኖር አይቻልም ። እንደዚህም ስለሆነ ቁስ አካል ነባር የሆነ ፤ ያለና በምርምር ሊታወቅና ሊደረስበት የሚችል ነገር ነው ።

ማቴሪያሊስትና አይዲያሊስት ለተባሉት ቃላት ብዙ ጊዜ የተጣመመ ትርጉም ተሰጥቷቸው ሰምተናቸዋል ። አንዳንድ አወናባጆች «ማቴሪያሊስት» ሲሉ አንድ ሰው ለገንዘብ ፤ ለሀብት ፤ ለቅንጦት ኑሮው የሚንገበገብ ፤ ጨካኝ ፤ ባልንጀርነትን የማያውቅ አውሬ አድርገው ያቀርቡታል ። ግን በፍልስፍና ትርጉሙ ከወሰድነው በሰው ታሪክ ውስጥ እየደጋገሙ የታገሉና ለፍትሕ ፤ ለሕዝብ ፍቅር ፤ ለሰላም ፤ የራሳቸውን የሰው ብዙ ማቴሪያሊስቶች እንዳሉ እናያለን ። በሌላ በኩል ደግሞ « አይዲያሊስት » ሲባል ለእምነቱ ፤ ለሐሳቡ ተጨባጭ ሀብቱንና ምቾቱን ትቶ እየተሠዋ የሚኖርና የሚሞት ከርታታ ያደርጉታል ። ነገር ግን በፍልስፍና ትርጉም እንዳየነው ከሆነ በሰው ዘር ታሪክ ውስጥ በአድኃሪነታቸውና በጭካኔያቸው የታወቁና ፍትሕን የሚቃወሙ ፤ ሕዝብን የሚጨቁኑ አይዲያሊስቶች ናቸው ። ለምሳሌ እነሂትለርንና ሞሶሎኒን ብንወስድ ፍልስፍናቸው አይዲያሊስት ፍልስፍና ነበር ።

ፈላስፋዎች እንግዲህ ከጥንት ጀምረው በነዚህ ሁለት ክፍሎች ተከፍለው ሲነታረኩና ሲፋጩ ይኸው እስከዛሬ አሉ ። ለመሆኑ ከመጀመሪያው ይህ የፍልስፍና መለያየት ከየት ፈለቀ ? እስከዛሬስ ለመዝለቅ እንዴት ቻለ ?

በመጀመሪያ ይህ ልዩነት የመጣው የሰው ዕውቀት እጅግ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ስለነበረ ነው ። ምክንያቱም ቀላሉ ፤ ዕውቀትን የማይጠይቀው ፤ አመሳክሩኝ ብሎ የማያስጨንቀው እምነት ሕሊናዊነት ስለሆነ ነበር ። በጥንት ዘመን ሰዎች ለምሳሌ መብረቅ ፤ ተራራ ፤ ዝናብ ፤ ከየት እንደመጡ ለማወቅ መመራመር ሲፈልጉ ፤ ሩቅ ሳይሔዱ ይደክማቸው ነበር ። ከነዚህም አስጨናቂ ጥያቄዎች ሁሉ የሚገላገሉት የማይታይ ፤ የማይጨበጥ ሁሉን አስተካክሎ የሠራ አንድ ነገር አለ በማለት ነበር ። በዚህ መልክ ሰዎች ድካማቸውን የሸፈኑ መስሏቸው አመሳክሩኝ የማይለውን የአይዲያሊዝም ወይም የሃሳባዊነት እምነት በየኅብረሰቡ እንዲስፋፋ ረድተዋል ።

ቀስ በቀስ ግን የሳይንስ መስፋፋት አይዲያሊዝምን እየኮረኮመ ስለሔደ ቁስ አካላዊነት ወይም ማቴሪያሊዝም ደግሞ የዚያኑ ያህል እየተስፋፋ መጣ ። ቀስ በቀስም የዕውቀት ብርሃን እየተስፋፋ ተፈጥሮም ምሥጢሯን እየፈለቀቀች በመግለጿ ስለሰላም ፤ ስለዝናብ ፤ ስለመብረቅ . . . አመጣጥ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ሊረጋገጡ የሚችሉ ተጨባጭ ሐቆች ተገኙ ። ማቴሪያሊዝምም ወይም ቁስ አካላዊነት ከዕውቀት ጋር አብሮ እየዳበረ ሔደ ።

ግን ሃሳባዊነት (አይዲያሊዝም) አሁንም ቢሆን ይታገላል እንጂ ጨርሶ አልሞተም ። ይህ የሆነበት ምክንያት ወደፊት እንደምናየው ኅብረተሰቦች በበዝባዥና በተበዝባዥ ከተከፈሉ ወዲህ ፤ በየመሥመሩ ስምምነት እየጠፋ በመሔዱ ፤ በፍልስፍና ሆነ በሞራል ፤ በፖለቲካ ሆነ በማንኛውም ኅብረተሰብ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ሰዎች የተለያዩ አስተያየቶች ስለሚከተሉ ነው ።

በተለይ በፍልስፍናው የሔድን እንደሆነ በእንደዚህ ዓይነቶቹ ኅብረተሰቦች የማቴርያሊዝም መስፋፋትና ማደግ ከአይዲያሊዝም ጋር እጅግ የመረረ ትግል የሚጠይቅ ነገር ነበር ። ለምን ? ምክንያቱም በኅብረተሰቡ ውስጥ በገዥው መደብ ብርታት ተደላድለው ፤ «አዋቂዎች» በሚባሉ «ትላልቅ» ሰዎች ቡራኬ አግኝተው የተጫኑትን እምነቶች ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ማጋለጥ ፤ እነዚህን «አዋቂዎች» እንደመቋቋም ስለሚቆጠር ገዥ መደብ የእንዲህ ዓይነቶቹን አስተሳሰቦች መስፋፋት ይቃወም ነበር ።

ግን ይህ ብቻ አልነበረም ። የሃሳባውያን ፍልስፍና ራሱ በታሪክ ተደጋግሞ እንደታየው የበዝባዦችን ፤ የድንቁርናንና ባሉበት ለመርገጥ የሚፈልጉ ሰዎችን ጥቅም የሚጠብቅ ፍልስፍና ነው ። ቁስ አካላዊነት ደግሞ ከዕውቀት መዳበር ጋር አብሮ የሚዳብር ፤ የሥልጣኔን መስፋፋት ፤ የብዝበዛን መወገድ የሚደግፉ ወገኖችን ጥቅም የሚያረጋግጥ ነው ። ሃሳባዊነት የተደላደለውን ወገን ፤ ቁስ አካላዊነት የታዳጊውንና የፈንቃዩን ወገን የሚደግፉ ፍልስፍናዎች ናቸው ።

በቁስ አካልነትም ሆነ በሃሳባዊነት ማመን በትግላችን ላይ የሚያመጣውን ልዩነት ጠለቅ ብለን ከማየታችን በፊት የነዚህን ሁለት ፍልስፍናዎች መሠረታዊ ይዘት አጠቃለን ወደማርክስ ፍልስፍና ሌላ አካል ወደ ዲያሌክቲክስ እንገባለን ።

በቁስ አካላዊነትና በሃሳባዊነት መካከል ሦስት ዋና ዋና ልዩነቶች አሉ ።
እነሱም ፤ —

አንደኛ— ሃሳባውያን ቁስ አካል የሃሳባችን ተቀጢላ ፤ የሕሊናችን ጥላ እንጂ ብቻውን የነበረ ያለና የሚኖር ነገር አይደለም ይላሉ ። ቁስ አካለኞች ግን ጠቅላላውን ቁስ አካል ሲባል ከሃሳባችን ውጪና ነፃ ሆኖ ያለ ነው ብለው እንዲያውም ሃሳብ የሚፈልቀው ከቁስ አካል ነው ፤ ሃሳብ ግን የቁስ አካል ተቀጢላ ፤ የቁስ አካል ጥላ ነው ብለው ያስተምራሉ ። በአጠቃላይ ሃሳባውያን ሃሳብ ቁስ አካልን /ማተር/ ፈጠረ ይላሉ ። ቁስ አካላውያን /ማቴርያሊስቶች/ ግን የለም ቁስ አካል ነው ሃሳብን ያመጣው ይላሉ ።

ሁለተኛ —ሃሳባውያን መንፈስና ሐሳብ ፤ከቁስ አካል ተነጥለው ለመኖር ይችላሉ እንጂ ቁስ አካል ከሃሳባችን ውጪ ምንም ዓይነት ህልውና ሊኖረው አይችልም ይላሉ ። ቁስ አካለኞች ደግሞ ቁስ አካል የሚባል ሁሉ ሰው ቢፈቅድም ፤ ባይፈቅድም ፤ ቢያውቀውም ባያውቀውም ያለ ነገር ነው ይላሉ ።

ሦስተኛ —ሃሳባውያን ምንም ስንመራመር ብንውል ሰው ሊያውቀው ከሚቻለው አድማስ ባሻገር ፤ ከሱ በላይ የሆነ ፤ በሳይንስ ሊረጋገጥ ከሚቻለው በላይ የሆነ በምርምር የማይደረስበት ነገር አለ ሲሉ ፤ ቁስ አካለኞች ደግሞ ዓለምና አካባቢዋ ነባር የሆኑ ተጨባጭ ህልውና ያላቸው በመሆናቸው ተመርምረው ሊደረስባቸውና ሊታወቁ ይችላሉ በማለት ለሰው ልጅ የምርምር ችሎታ ወደር የማይገኝለት እምነታቸውን ይገልጻሉ ።

የማርክስ ፍልስፍና ቁስ አካላዊ ብቻ ሳይሆን ዲያሌክቲካዊም ነው ። ይህም ማለት አካባቢውን ሁሉ ሲያጠና በማያቋርጥ እንቅስቃሴ ፤ እድሳትና ዕድገት ላይ እንደሆነ እየተረዳ ነው ። የሚቀጥለው እትማችን ስለ ዲያሌክቲካዊ የምርምር ስልት ይሆናል ።

---

## ማ ሳ ሰ ቢ ያ

ለተወደዳችሁ የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ጋዜጣችን አንባቢዎች ሁሉ ፤ ጋዜጣዋን ከየክፍለ ሀገሩ የጋዜጣ ማከፋፈያ በተመሳሳይ ዋጋ መግዛት የምትችሉ ስለሆነ ፤ ገንዘብ በኛ በኩል መላክ እንድታቆሙና ከዚያው ለማግኘት እንድትሞክሩ እንገልጻለን ።

«አብዮታዊት ኢትዮጵያ »